DCRA

DEPARTMENT OF CONSUMER & REGULATORY AFFAIRS

# ስለ ሽያጭ ጥያቄና መልሶች

## በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ስለ ሽያጭ በአብዛኛው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### የሽያጭ ጊዜያዊ እገዳ

**የሽያጭ ጊዜያዊ እገዳው ምንድን ነው?**

የዲሲ ምክር ቤት Department of Consumer and Regulatory Affairs ወይም DCRA (የተጠቃሚና የቁጥጥር ጉዳዮች ዋና ክፍል) ከ1998 ጀምሮ የመንገድ ላይ ሽያጭ ፈቃድ እንዳይሰጥ የሚከለክል ሕግ ወይም እገዳ አስተላልፎ ነበር።

**እገዳ ለምን አስፈለገን?**

ከ3000 ሻጮቹ ውስጥ አብዛኞቹ የሚወዳደሩት ለአንድ ዓይነት ቦታዎች ነበር። አንዳንድ ሻጮች ይፋ ያልሆነ "መጀመሪያ የመጣ መጀመሪያ ይጠቀም" ሕግ ሲከተሉ ሌሎች ደግሞ ይፋ ያልሆነውን ሕግ በሚከተሉት ሻጮች ተገፍተው ለቀው እንዲሄዱ ተገድደው ነበር። ሻጮች የሕዝብ ቦታ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው የተሻለ፣ የሚያስተማምንና በይበልጥ ማስከበር የሚቻል ስርዓት ለዲሲ ያስፈልግ ነበር።

**በወቅቱ ስንት ሻጮች ፈቃድ አላቸው?**

670 ሻጮች አካባቢ አሁን ፈቃድ አላቸው።

**እገዳው መቼ ያበቃል?**

የሽያጭ እገዳው ኦክቶበር 15 ያበቃል።

አዲሱ ሕግ DCRA አዲሱን የሽያጭ ፕሮግራም በሥራ ላይ እንዲያውል 90 ቀን ሰጥቶታል። በ90 ቀን ጊዜ ውስጥ DCRA አዲሱን ፕሮግራም አሁን ፈቃድ ላላቸው ሻጮችና ፈቃድ ማውጣት ለሚፍልጉ ሰዎች ያስተዋውቃል።

DCRA አዲሱን የሽያጭ ፕሮግራም ደረጃ በደረጃ ይጀምራል።

### ደረጃ ያለው ዕቅድ

**ደረጃ ያለው ዕቅድ ምንድን ነው?**
ደረጃ ያለው ዕቅድ ማለት የሽያጭ ቦታዎችን ማወቂያና የአቀማመጣቸውን ካርታ የማውጣት ሂደት ነው። አራት ደረጃዎች አሉ፤

1. አሁን ፈቃድ ያላቸው ሻጮች (በከተማው ሁሉ)
2. ዳውንታውን ቢዝነስ ኢምፕሩቭመንት ዲስትሪክት ወይም BAD (የዳውንታውን ንግድ ማሻሻያ አውራጃ)፣ የዳውንታውን DC 120 ብሎክ የያዘ አካባቢ ኤፍ ስትሪትን ጨምሮ፣ 14th Street እና Pennsylvania Avenue ከ Freedom Plaza አቅራቢያ ያለው)
3. የሴንትራል ቢዝነስ ዞን በሙሉ (K Streetን ጨምሮ ከ Georgetown እስከ Union Station)
4. በከተማው ሙሉ (የዞን ማውጫ ሕግ የሽያጭ ፈቃድና የሕዝብ ክልል የፈቃድ ወረቀት የሚፈቅድበት ቦታ ሁሉ)።

### የሽይጭ ደረጃዎች አጭር መግለጫ

በአዲሱ ሕግ መሠረት DCRA አዲሱን የሽያጭ ፕሮግራም በሥራ እንዲያውል 90 ቀን ተሰጥቶታል።

**1ኛ ደረጃ**

ከኦክቶበር 15 2006 እስከ ጃኑዋሪ 14 2007

አሁን ፈቃድ ያላቸው ሻጮች ላሉበት ቦታ ከዲፓርትመንት ኦፍ ትራንስፖርቴሽን ወይም DDOT የሕዝብ ቦታ ፈቃድ እንዲያወጡ ዕድል እየሰጠን ነው።

**2ኛ ደረጃ**

ካጃኑዋሪ 15 እስከ ጁላይ 14 2007

ከማክሰኞ ጃኑዋሪ 16 2007 ጀምሮ አመልካቾች የሽያጭ ፈቃድና የሕዝብ ቦታ ፈቃድ ማውጣት ይችላሉ። DDOT ለዳውንታውን BAD አካባቢ (የዳውንታውን ዲሲ 120 ብሎክ አካባቢ፣ F streetን ጨምሮ፣ 14th Street እና Pennsylvania Avenue ከ Freedom Plaza አቅራቢያ ያለው) የሕዝብ ቦታ ፈቃድ ይሰጣል።

**3ኛ ደረጃ**

ከጁላይ 15 እስከ ዲሴምበር 31 2007

ከሰኞ ጁላይ 16 2007 ጀምሮ የሽያጭ አመልካቾች የሽያጭ ፈቃድና የሕዝብ ቦታ ፈቃድ ማግኘት ይችላሉ። DDOT ለኮምፐሊት ሴንትራል ቢዝነስ ዞን (ከጆርጅታውን እስከ ዩኒየን ስቴሽን ድረስ ላለው K Streetን ጨምሮ) የሕዝብ ቦታ ፈቃድ ይሰጣል።

**4ኛ ደረጃ**

ከጃኑዋሪ 1 እስከ ኤፐሪል 30 2008

ከረቡዕ ጃኑዋሪ 2 2008 ጀምሮ የሽያጭ አመልካቾች የሻጭ ፈቃድና የሕዝብ ቦታ ፈቃድ ማግኘት ይችላሉ። DDOT ለከተማው ሁሉ የሕዝብ ፈቃድ ይሰጣል።

## የሽያጭ ፈቃዶች

**የሽያጭ ፈቃዶች የሚሰጠው ማነው?**

- DCRA የሽያጭ ንግድ ፈቃዶች ይሰጣል።

**አንድ ሻጭ ፈቃድ ለማግኘት ሌላ ምን ያስፈልገዋል?**

- ሻጩ ለሚመርጠው ቦታ የዲፓርትመንት ኦፍ ትራንስፖርቴሽን ወይም DDOT (የመንገድ መጓጓዣ ዋና ክፍል) የሕዝብ ቦታ ፈቃድ ይሰጠዋል። የDDOT የሕዝብ ቦታ የፈቃድ ወረቀት የሻጩን ትክክለኛ ቦታ ያሳያል።

- እያንዳንዱ አመልካች ከሜትሮፖሊታን ፖሊስ ዲፓርትመንትና ከ ኦፊስ ኦፍ ታክስ ሬቬኑ የክሊን ሃንድስ ሰርቲፊኬት ማውጣት አለበት።

- አመልካቹ ምግብ የመሸጥ ሐሳብ ካለው/ካላት ለሻጭ ፈቃድ ከማመልከቱ/ቷ በፊት ከዲፓርትመንት ኦፍ ሄልዝ ወይም ዲኦኤች የጤና ሰርቲፊኬት ማውጣት አለበት/አለባት።

**ሻጮች መቼ ነው ፈቃድ ማግኘት የሚችሉት?**

በአዲሱ የሽያጭ ሕግ መሠረት ሻጮች በዲስትሪክቱ ውስጥ ከመሸጣቸው በፊት የሽያጭ ፈቃድና የሕዝብ ቦታ ፈቃድ ማውጣት አለባቸው።

አሁን ፈቃድ ያላቸው ሻጮች ላሉበት ቦታ አዲስ ፈቃድና የሕዝብ ቦታ ፈቃድ ማመልከት ይችላሉ።

DCRA ለእነዚህ ቦታዎች ካርታ እያወጣ ነው። ይህ ካርታ እስከ ጃኑዋሪ 14 2007 ያልቃል።

የሽያጭ ፈቃድዎንና የሕዝብ ቦታ ፈቃድዎን ለማግኘት ማክሰኞ ጃኑዋሪ 16 ቀን 2007 ማመልከት ይችላሉ።

አሁን ሻጭ የሆኑ ሰዎችንና ወደፊት ሻጭ መሆን የሚፈልጉ ሰዎችን ሥራ ላይ የማዋያ ጊዜውን ተጠቅመው ጠንካራ ንግድ እንዲመሰርቱ እናበረታታለን።

- የንግድ ንድፍዎን ያውጡ፣ መነሻ ገንዘብ ይፈልጉ፣ የጅምላ ሻጮች ያግኙ እና ተጠቃሚውን ሕዝብ ይወቁ።

- ዲስትሪክቱ የሚሰጣቸውን መረጃዎች ይጠቀሙ - በተለይም የቢዝነስ ሪሶርስ ሴንተሩን። በይበልጥ ለማወቅ በኢንተርኔት http://brc.dc.govን ይጎብኙ።

- Martin Luther King Jr. Memorial Library, 901 G Street NW, አንደኛ ፎቅ (202) 727-2241 ላይ የሚገኘውን የኢንዛንስድ ቢዝነስ ኢንፎርሜሽን ሴንተር ወይም EBAC ይጎብኙ። በይበልጥ ለመረዳት በኢንተርኔት http://restoredc.dc.gov/ebic ይጎብኙ።

- የEBAC የትምህርት ክፍሎች ይውሰዱ።

## ቦታ

**ቦታዎች የሚወሰኑት እንዴት ነው?**
እያንዳንዱ ሻጭ ቦታውን ወይም ቦታዋን ይመርጣል/ትመርጣለች።

DCRA DDOT የትኞቹ ቦታዎች ክፍት እንደሆኑ ለሻጮች ያስረዳሉ።

**DCRA የሽያጭ ፈቃዱንና ቦታውን ለማያያዝ ለምን ወሰነ?**

DCRA ምን በደንብ እንደሚሠራ ለማወቅ ሰባት ከተማዎችን አጠና - አትላንታ፣ ቦስተን፣ ሺካጎ፣ ማያሚ፣ ኒውዮርክ፣ ፊላዴልፊያና ፖርትላንድ ኦሬገን።

DCRA ከጥናቱ ምን አገኘ?

- ሌሎች ከተማዎች እገዳ በደንብ እንደማይሠራ ተገንዝበዋል።

- ሌሎች ከተማዎች የሽያጭ ፈቃዶችን ከሻጭ ቦታዎች ጋር በማያያዝ ጥሩ ውጤት አግኝተዋል።

- የብዙ የሌሎች ከተሞች ሻጮች ሰፋ ያለና ብዙ የተለያዩ የምርት ዓይነቶች ያቀርባሉ - በተለይም መንገድ ላይ የሚሸጡ ምግቦች።

## በይበልጥ መረጃ ለማግኘት

- ኦክቶበር 10፣ 12፣ 13፣ 16 ወይም 17 ከምሽቱ 6 ሰዓት እስከ 8 ሰዓት በኦልድ ካውንስል ቼምበርስ ውስጥ በአድራሻ 441 4th Street NW የሚሰጥ የሽያጭ ገለጻ ተካፋይ ይሁኑ።

  ኦክቶበር 16 የሚሰጠው የሽያጭ ገለጻ የኮሪያን ቋንቋ አስተርጓሚ ይገኝበታል።

  ኦክቶበር 17 የሚሰጠው የሽያጭ ገለጻ የስፓኒሽ ቋንቋ አስተርጓሚ ይገኝበታል።

  የአማርኛ፣ የቻይንኛና የቪዬትናምኛ አስተርጓሚዎች የሚገኙባቸው የሽያጭ ገለጻዎች በቅርቡ ይጀመራሉ።

- ኦክቶበር 19 ከቀኑ 2 ሰዓት እስከ ምሽቱ 8 ሰዓት በ Martin Luther King Jr. ላይብሬሪ በሚደረገው የሽያጭ ዝግጅት ላይ ተገኝተው ፈቃድ ለማውጣት እንዴት እንደሚያመለክቱ፣ ስለ ምግብ፣ ሸቀጣሸቀጥና የዕቃ ጋሪ ደንቦችና የንግድ ንድፍ ለመጻፍ የት እርዳታ ማግኘት እንደሚችሉ ይወቁ።

- አዲስ መረጃ ለማግኘት dcra.dc.govን ይጎብኙ።

- ጥያቄዎች ካልዎት በስልክ ቁ(202) 442-4512 ይደውሉ